# እስኪ ጀግና እንሁን

በአምባገነኖች እብሪት
በፍትሕ አልባ ሥርዓት
በዲሞክራሲ እጦት
በረሀብና እርዛት
ስንማቅቅ ለዘመናት
የአንድነት እትብታችን
ሲበጣጠስ ሊበታተን
ከሀዲው የመለስ ቡድን
ሲዘርፍ ሲያዘርፈን
ወደብ አልባ ስንሆን
ስንት ጀግኖቻችን የተሰውበትን
ኧረ ሚስጥሩ ምን ይሆን
ያደነዘዘን ያፈዘዘን
ስቃያችን ያላስቆጣን
መከራችን ያላስቆጨን
ኧረ ያገር ያለህ
ኧረ የወንድ ያለህ
ተነስ ያገሬ ልጅ
ተነስ የወንዜ ልጅ
እስቲ ቁጭት ይግባህ
ያባትህ ልጅ ወንድ ሁን
ለማስፈን ፍትህን
ለመሥራት ታሪክን
ከንግዲህ በል ይብቃን
እንነሳ ሆ ብለን
ምእራብ ምስራቁን ይዘን
ከደቡብ እስከሰሜን
እጅ ለጅ ተያይዘን

በአንድነት ሕብረት ፈጥረን
በጽኑ አቋም ተደራጅተን
እንውጣ አደባባይ መፈክራችንን ይዘን
እንዘምር ፍትሕን
ዲሞክራሲ ነጻነትን
እንበል በቃን በቃን
አሜን ብሎ መኖርን
መለስና አጋሮቹን
እንቅፋት ለሆኑብን
ለአንድነት ለእድገታችን
እንንገራቸው አስረግጠን
እስከየት እንደሁ ጽናታችን
ቃለምሀላ እንደገባን
ዱር እስከሚሆን መዋያችን
ጫካ እስከሚሆን መኖሪያችን
ይወቁት ቁርጣችንን
እናሳያቸው ትግሉን
ተስፋ እማንቆርጥ መሆኑን
እስከምንጎናጸፍ ድሉን
ወገኖቼ ኢትዮጵያውያን
እንታገል ጀግና እንሁን
እንክፈል መስዋዕትን
የቁርጥ ቀን ልጆች እንሁን
ለችግሯ ደራሽ እንሁን
ለእምዬ ኢትዮጵያችን
እንድናልፍ ታሪክ ሠርተን (2x)
ለመጪው ትውልዳችን (2x)

## ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ

ዓለማየሁ ሽመልስ
ሚያዝያ 1 ቀን 2003